በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Accounting and Auditing Board of Ethiopia

ቁጥር ኢሂአቦ/939/12
Ref.No
ቀን 18/12/2012
Date

የገቢ ደብዳቤ
የተዘፈበት ቀን 18/12/2012
የተላከበት ቁጥር ኢሂአቦ/939/12
የደረሰበት ቀን 19/12/2012

ለኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት

አዲስ አበባ

**ጉዳዩ፡ የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ እና የሪፖርት አቅራቢዎች መለያ መስፈርት ስለመሻሻሉ**

መንግስት ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ሥርዓት በመዘርጋት የተመቸ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ከባቢ በመፍጠር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የሚኖረውን ከፍተኛ ጠቀሜታ፣ እንዲሁም የተጠናከረ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ሙያ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለመደገፍ፣ ለማበረታታት እና ለማረጋጋት የሚጫወተውን ቁልፍ ሚና በመገንዘብ በሀገር ውስጥ በሚገኙ በግል እና በመንግስት ዘርፍ ባሉ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘዉ አዋጅ ቁጥር 847/2006ን እና አዋጁንም ለማስፈፀም "የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ" ማቋቋሚያ ሥልጣን እና ተግባሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007ን አውጥቷል።

በአዋጁ አንቀፅ 5/1 ላይ ተፈጻሚነት የሚኖራቸዉ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች በማለት ዓለም አቀፉ የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች ቦርድ ያወጣቸዉን፡

ሀ/ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች፣

ለ/ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች እና

ሐ/ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ዓለምአቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎችን እንዲተገብሩ ተደንግጓል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 4/2/መ/ ቦርዱ ሪፖርት አቅራቢ አካላትን የህዝብ ጥቅም ያለባቸዉ አካላት ወይም አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ መለየት የሚያስችል መስፈርት እንደሚያወጣ እና በአዋጁ አንቀጽ 8/1 ማንኛዉም ሪፖርት አቅራቢ አካል ቦርዱ በሚያወጣዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሪፖርቱን ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለበት ተደንግጓል።